# <u>ሳይብስ ወደ ፀበል፤ አቶ እያሱ</u> ግንቦት 21, 2006 ዓ.ም.

*ለ "ኢሕአፓና ታሪኩ" ከ - - እያሱ ዓለማየሁ፤ ምላሽ ከ ጉዱ ካሣ*

"ኢሕአፓና ታሪኩ" በሚል ርዕስ ቀን ያልተፃፈበትን ባለ 8 ገጽ ጽሁፍ በአቶ እያሱ ዓለማየሁ የተፃፈውን ከአሲምባ ድረ ገጽ ላይ ወስጄ አነበብሁና ለማውቀውና እሳቸውንም ለሚያውቃቸው አንድ ወዳጄ "ምነው እኝህን ሰው ሳይብስ ወደ ጠበል ብትወስዷቸው አልኩት" ሳቅ አለና "አይ ጉዱ አቶ እያሱ እንኳን ፀበል ውቅያኖስ ቢከተቱ የያዛቸው አባዜ አይለቃቸውም፤ አሁንማ ብሶባቸዋል" አለኝ።

ደጋፊና አፍቃሪ ኢሕአፓዎችን ሳይቀር ሁሉንም እየነደፉ የኢሕአፓ አባልም መሪም ሆነው ብቻቸውን የቀሩት አቶ እያሱ የሚነግራቸው ያጡ ይመስላሉ። እርግጥ ሰውየው ከተጠናወታቸው አምባገነናዊ ባህሪ አንፃር አለመስማታቸው ስለሆነ እርቃናቸውን ያስቀራቸው ጽሁፋቸውን ላነበቡ አንባቢዎችና ለሌሎችም መልዕክት ይሆን ዘንድ ነው የዚህ ጽሁፍ ዓላማ። የእሳቸው ጆሮ "ቀዳዳ ጨረቃ" ብለው እፃፉት መፃህፋቸው ግድግዳ ላይ ተጣብቋል። አሁን የቀረው ምላሳቸውና ብዕራቸው ነው። ጆሮ የሌለው ፀሐፊ ቢሆኑም ማንበብ ይችላሉ ብዬ ነው የፃፍኩላቸው። አንዳንዴ ጽሁፋቸው ውስኪን እንደ አምቦውኃ እየጠጡ የሚሞነጫጭሩት ይመስለኛል።

አቶ እያሱ ስለ ኢሕአፓ ማን ተናግሮ? ስለ ኢሕአፓ ማን ጽፎ? ስለ ኢሕአፓ ማን አድምጦ? ስለ ኢሕአፓ ማን አልቅሶ? ስለ ኢሕአፓ ማን ስቆ? ስለ ኢሕአፓ ማን ሞግቶ? ስለ ኢሕአፓ ወዘተ....ወዘተ....ወዘተ.... ይሉናል። ታዲያ ይህ እብደት፣ ህመም፣ ጤና ማጣት፣ መረበሽ፣ ተስፋ መቁረጥ አይደለም ትላላችሁ። እንዴታ! እሳቸው ስለ ሌላው ሲጽፉ ሲያብጠለጥሉ መብታቸው ነው፤ እሳቸው ሌላውን "እኔ ብቻ ባይ" ሲሉ ልክ ናቸው፣ የእሳቸው ብዕር ብቻ ነው ዕትብቱ ከእውነት ጋር የተጣበቀው፤ የተዛመደው።

አሁን አሁንማ ኢሕአፓን ነቅፎ አይደለም በትክክልም ስለ ኢሕአፓ የሚጽፈውንና የሚሞግተውንም በእኔ ቁጥጥር ሥር ካልሆንክ/ሽ ምን አግብቶህ/ሽ መልዕክታቸው የሕመምና ጤና ማጣት ምልክት ስለሆነ ሚሻላቸው ከሆነ የሰው ምክርስ አልሰሙምና ዘመድ ነኝ ባይ ካለ ሳይብስ ወደ ፀበል ቢወስዳቸው ጥሩ ነው።

ኢሕአፓ እራሱን ለሕዝብ ይፋ ካደረገበት ነሐሴ መጨረሻ 1967 ዓ.ም. ጀምሮ በከተማ በቀይ ሽብር እስከተመታበት፣ በሜዳው እስከብተናው በአለው ሂደቱ ብቻ እንኳ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ ክልል ሳይገድበው አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል አሰልፎ አታግሏል። በዚህ ሂደቱ ላይ ከጠላት ምት ጨምሮ ራሱ በሰራቸው ስህተቶች ከዛሬ ነገ ሥልጣን ይዞ የሕዝብንና የሀገርን ጥያቄ መለሰ የተባለለት ፓርቲ ዛሬ ሂሳብ አዋቂዎቹ Imajinery lines (የሀሳብ መስመር) ወይም Imajinery numbers (የሀሳብ ቁጥር) እንደሚሉት Imajinery Party (የሀሳብ ፓርቲ) ሆኗል ቢባል ለሌሎች እንጃ እንጂ ለዚህ ፀሐፊ ታይቶታል። ታዲያ አንባቢ ሊረዳልኝ የምፈልገው በሂሳቡ ዓለም Imajinery lines ም ሆነ Imajinery numbers ከተሠራባቸው እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው እና ኢሕአፓም የማይታይ ግና ቢሠራበት እጅግ

ጠቀሜታ ያለው ፓርቲ ነው ለማለት ነው ምሳሌውን የሰጠሁት። ከዚህ በላይ ማስረዳት ይከብደኛልና አትጨነቁበት ዝለሉት።

ኢሕአፓ በዚህ ጉዞው የሕዝብ ፓርቲ ነው ካልን ታሪኩም የሕዝብ ነው። አቶ እያሱ ዐደዋን ለምኒልክ ማን ሰጠው? የህዝብ ነው፣ መተማን ለዮሐንስ ማን ሰጠው? የሕዝብ ነው ወዘተ ካሉ ኢሕአፓንስ ለርሶ ማን ሰጠዎት የሕዝብ ነው! እንላለን። እባክዎ፤ እስቲ ባልተበረዘ አእምሮዎ ያስቡት። እውን እነ ጵውሎስ ኞኞ ዐድዋ ዘምተው ከምኒሊክ ጋር አድገው ነው ስለ ዐድዋ ታሪክ ያስነበቡን? "በእኔ ኢሕአፓ የሌለ ስለ ኢሕአፓ መፃፍ አይገባውም" ሲሉ በዐድዋ ጊዜ የነበሩ ዛሬ የሉምና መፃፍ መቆም አለበት የፃፉትም በዐድዋ ጊዜ የሌሉ ከሆነ መጽሐፋቸው ወደ ቆሻሻ እያሉን እንደሆነ የፃፉትን ጽሁፍ እየተረጎምኩሎት ነው፤ እና እኚህ ሰው እኚህ የትግል ምሁር እውን ጤና ናቸው? እንጃልኝ።

አቶ እያሱ እስከዛሬ የተፃፉትን ስለ ኢሕአፓ ያብጠለጥላሉ፤ በተለይ ቢያዩ ቢመለከቱ ምንም ጠብ የሚል ስለ ኢሕአፓ ታሪክ በሚገባ የተፃፈ ባለመኖሩና በተለይ የደርግ ኢሠፓ ኃይሎች ብርታትና ጉልበት አግኝተው ኢሕአፓን ጥላሸት እየቀቡ ሲጽፉ የታዘቡ የኢሕአፓ ልጆች የሚያውቁትን እንኳ ማስነበቡ የኢሕአፓን ታሪክ በትንሹም ቢሆን ለአሁኑ ትውልድ ጭላንጭል ይሰጣል፤ ይሆናል ብለው የሚለፉትን ያብጠለጥላሉ። በፍኖተ ሬድዮ ይረግማሉ።

በተለይ የኢሕአፓ አባል የነበሩና በድርጅቱ መመታት፣ መዳከም፣ በሌላም ምክንያት ፓርቲውን የተለዩ መፃፍ አይደለም በሚጽፉት ላይ እንዴት አስገቡተውት ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት እውን ስልጣን ቢይዙ የት እንደሚደርሱ ቆም ብለው አስበውታል?

ማንም የሚጽፈው መጽሐፍ ስለ ኢሕአፓም ሆነ ስለ ሌላ፣ እውነተኛ ታሪክም ይሁን ልብ ወለድ የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎን ይኖረዋል። ለምን ፃፋችሁ ብሎ መንደፍ ሳይሆን እዚህ ጋ ተሳስታችኋል ብሎ ማረም እዚህ ጋ ጥሩ ነው ብሎ ማበረታታት እንኳን ኢሕአፓን 36 ዓመት ሙሉ ከመሩት የዕድሜ ባለፀጋ ይቅርና  ተራ አባል ከነበርነው የኢሕአፓ ልጆች አይጠበቅም።

እንደው ባይያያዝም አንድ ነገር ትዝ አለኝና ላንሳው፤ መቼም የአቶ ኢያሱ ነገር ሲነሳ አንዳንዴ ያስቁኛል እውነት የሚያደርጉት ኢሕአፓን ከመውደድ ከሆነ አሳበዱት እንጂ አልጠቀሙትም። ጃንሆይ ጃጁ ሥልጣን ይልቀቁ ብለው ታገሉ፣ ደርግን እንኳ እዚህ ጋ አላስገባም ፋሽስት ነውና፤ መለስ ግና ዴሞክራት ነኝ እያለ የምርጫ ፖለቲካ ማታለያው ስለነበር "ሥልጣን ሙጭጭ ብሎ የያዘ" እያሉ ይወቅሱት ነበር። እርሶስ? የሰለቸ መልሶ አባላት እየመረጡኝ ነው የሚለውን እንዳይደግሙልኝ እንደው በማርክስ ይዞታለሁ፤ በእርሶ ሲሆን ምናለበት? ኢሕአፓ እኮ ነው ሊሉን ነው?

ሌላ ልጨምር በወያኔ ዘመን በተከታታይ ለስምንት ዓመት የሀገሪቱ ፕሬዘዳንት የነበሩት መቶ አለቃ ግርማ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ አባት ቢሆኑ አቤት! አቤት! እንዳው ዝም ነው። እንዴት ፈረደበት፣ እንዴት ተጨማሪ መፃፊያ አገኙ፣ እንዴት እንደሚያብጠለጥሉት ሁሉም ይረዳዋል። የእርሶ ባለቤት አባትነታቸው ግን ምንም አይደል? እኔም እስማማለሁ የእርሶ

ቢያጠራጥረኝም ባለቤቶ የዓላማ ሰው ስለሆኑ፤ አእምሮዎ ትምህርት ተቀባይ ከሆነ እንዲማሩ የምፈልገው የእርሶን ባለቤት አባት የወያኔ ፕሬዘዳንት በመሆናቸው ከወያኔ ጋር ሊኖር የሚችል ግንኙነትን አንድም ሰው አንስቶ አለመተቸቱን ነው። ገባዎት?

በባህላችን ቡናም እስከ ሶስተኛ ይጠጣልና የመጨረሻ፡ ዛሬ ወዴት እንደገቡ ባላውቅም ወ/ሮ ብርቱካን ሚዴቅሳን "እንዴት አድርገው ፈርመው ከወያኔ እሥር ቤት ይወጣሉ" ብለው ቁም ስቅላቸውን ሲያሳያቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ብቻ ሳይሆን ምስጋና ለዓለማችን ሥልጣኔ ይግባውና በመረጃ ደረጃ ያለ ነው። የርሶ ባለቤት ወ/ሮ ገነት ግርማና ፍቅር በነበራችሁ ጊዜ አማካሪዎ የዲሲው አቶ መስፍን ተፈራ ከወያኔ እስር ቤት ፈርመው የወጡት ምን ነበር? እንዴት ነበር? ለእርሶና ለአሽመደመዱት ኢሕአፓ ሲሆን ጥያቄው የጠላት ነው? በዚህ ሂደት የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ያለው የኢሕአፓ ልዑካን ቡድን ፈሪ ሆኖ ፈርሞ ሲወጣ "ፈልፋሻና ዓላማ የለሽ" የተባሉት የመኢሶኑ ልዑክ አቶ አበራ የማነ አብ አላደርገውም ብለው 18 ዓመት ማቀው ሲፈቱ እንዴት ያዩታል? የተረገመ ፀሐፊ ነውና ዛሬ ያገኘችዎት ሀቁን በውስኪም ቢሆን ያወራርዱት።

እጅግ ብዙ ሊፃፍ ይቻል ነበር በእርሶ አፃፃፍ ከሆነ፤ የራሱ ደካማ ጐኖች ቢኖሩትም ያን የሕዝብ ፓርቲ ማሰደብ ይሆናልና ለወደፊት ጊዜ የሚያወጣው በርካታ ድብቅ ታሪክ እንደሚኖር የሚያውቁ በርካታዎች መኖራቸውን እንዲረዱ ነው ጠቀስ ጠቀስ የተደረገሎት። ማንም አያነበኝም፣ ማንም አያደምጠኝም፣ ማንም አይሰማውም፣ ማንም አይገባውም ብለው አይድከሙ። "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንዲሉ" እርሶ ስልጣን ቢይዙ ምን ጉድ እንደሚመጣ እየነገሩን ነው። ይህን የምለው ለዚህ ፀሐፊ እርሶ በኢሕአፓ ስም ፓርቲውን ሲያሽመደምዱና ለጠላት ሲያመቻቹ የኖሩ፤ የፓርቲውን ጥሩ ጎን በመጥፎ ስሙ የሳሉ ዛሬ ሁሉም እርቆት ቀና ማለት የተሳኖት፣ አንገት ደፍተው ሌሎችን አንገት ሊያስደፉ የሚጥሩ መሆኖት እንዲታወቅ ያስፈልጋል።

ዘለልኩና ወደ ሌላ ሄድኩ ደራሲ ቆንጂት ብርሃን "ምርኮኛን" ብታስነብብ "ወያኔ" ብላችሁ ልታብጠለጥሉ ከጅኗችሁ የአንባቢው ቁጥርና አፍቃሪ መጽሐፏ ሲበዛ ፍሬን መያዛችሁ የትላንት ሥራዎ ነው፣ አቶ አስማማው የኢሕአሠ ታሪክ ቁጥር አንድ መጽሐፉን ለምን አወጣብን ብለው አብጠለጠሉ፣ የሚገርመው ደግሞ ምን እንደፃፈ ያላነበቡትን የኢሕአሠ ታሪክ ቁጥር ሁለት እንኳ የድፍረቶ ድፍረት አናንቀዋል፣ የአቶ ካሕሳይ አብርሃን "የአሲምባ ፍቅር" ወያኔ ብለውታል፣ የሕይወት ተፈራን Tower In The Sky መጽሐፍ እንዲሁ እረሽነውታል፣ ስም ባይጠቅሱም በቅርብ የወጣውንም የአቶ ሰሎሞን ገ/ሥላሴን መጽሐፍ በሌለበት ይዋኛል ይላሉ። ይልቅስ የነዳፊ ዋናተኛ እርሶ አልሆኑም? ምነው ማር አልጥም አልዎ? እነኚህ ሁላ ጸሐፊያን ምንም ቢሆን ያበረከቱት በጎ ጐኑ ይበልጣልና በርቱ የሚለው ቃሎ ምነዋ ከአንደበቶ ጠፋ? ምነዋ ከብዕሮ ተጣላ?

የኢሕአፓ ታሪክ የሚነገረውም የሚፃፈውም ለእርሶ ተብሎ አይደለም። የኢሕአፓ ታሪክ ብዙዎች ጋ ያለ የሕዝብና የሀገር ታሪክ ነው። በከተማ በየቀበሌውና በየከፍተኛው የተደረጉ የኢሕአፓ ብርቅዬ ታሪኮችና የገዳዮችና የፋሽስቶች የማንነት ታሪክ በሚያውቁ ቢፃፍ

ምንድነው ችግሩ? በአለፈው ሳምንት እዚህ አሜሪካ ውስጥ 22 ዓመት ፍርዱን የተከናነበው የከፍተኛ 15ቱ ካድሬ ከፋለኝ ዓለሙን ታሪክ ስሰማ ምናለ የሚያውቁ ቢጽፉት ነው ያልኩት፤ እና ይህ ታሪክ የኢሕአፓ ነው ቢፃፍ ምናለ? በየክፍላተ ሀገሩ የነመላኩ ተፈራ ግድያና የጎንደር ልጆች ተጋድሎ፣ የነጌታቸው ሽበሺ ጨካኝነትና የሐረርጌ ኢሕአፓዎች ታሪክ፣ ሽረ ስንቱ ከኢሕአፓ የወጡ አሁን ኢሕአፓ መኖሩም የተዘነጋቸው ታሪኩን ቢያስነብቡን ምንድነው ክፋቱ? ኢሕአፓ ውስጥ ከሌላችሁ እንዴት ተደርጎ? እንዴት ታስቦ? ማለት እውን የጤንነት ነው? ምነዋ የነገሌን ኢሕአፓዎች ታሪክ ወያኔ እንደገባ አዲስ አበባ ገብቶና ወደ ትውልድ ቦታው ሄዶ ውብ የሆነች ወደ መቶ ገጽ የያዘች "ያልታደለው ትውልድ" መጽሐፍን ያስነበበንን አብዱ አብዱላሂን መጽሐፍ "ኢትዮጵያ" በሚለው በዲሲና አካባቢው እየታተመ በሚወጣው ጋዜጣችሁ ታወጡታላችሁ? ይህ በጐ ተግባር ነበር ከናንተ የሚጠበቀው። የሌሎችንም በዚህ መልኩ እየቆነጠቡ ማስነበቡ፣ ላልደረሰው ማዳረሱ፣ መደጋገሙ ይበልጥ ጠቀሜታ አለውና።

ስለ ኢሕአፓ ታሪክ የሚጽፉትን ከእነ ስህተቱም ቢሆን ማበረታታት፣ ሌሎች ይጽፉ ዘንድ መገፋፋት ይህ ነበር ተገቢው። ከጽሁፎ እንደተረዳሁት ግና በሕይወት ውብ አተራረክና አፃፃፍ፣ በቆንጂት ማራኪና፡ ያማረ ልብ ወለድ ትረካ፣ በአቶ ክፍሉ ያ ትውልድ ቅጽ 1,2,3 የኢሕአፓ እውነተኛ ታሪክ መጽሐፍ፣ በአቶ አስማማው ሁለት ቅጽ ኢሕአሠ አፃፃፍ ውበትና አገላለጽ (ሁለተኛው መንገድ ላይ ቢሆንም) የተናደዱና ሌላ ሚፃፍ ያለቀብዎት መሰለኝ። ተሳስተዋል! ልክ አይደሉም! አቶ እያሱ።

እንኳን የበርካታ ታሪኮች ባለቤት የሆነው ኢሕአፓ ይቅርና ስለ አንድ ሰው ታሪክ ፀሐፊዎች ከተለያየ አቅጣጫ ያስነብባሉ። አንዴ ተፃፈ አበቃ ተደመደመ ማለት አይደለም። ለምሳሌ፦ የሴቶች ጥያቄና ኢሕአፓ ብቻውን፣ የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄና ኢሕአፓ ብቻውን፣ የፖለቲካ ድርጅትና ኢሕአፓ ብቻውን፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ሠራተኞች ታሪክና ኢሕአፓ ብቻውን. . . ወዘተ በሚሉ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች እንኳ በርካታ መጽሐፍት ሊወጡ ይችሉ ነበር። ግና አላደለንም። እውነት ልንገርዎና እንደፉከራዎ ስለ ኢሕአፓ ታሪክ በግሎም ሆነ በጋራ አንድም መጽሐፍ እንደማያወጡ። "የአህያ ውኃ ጠጪ እንዲሉ" አድፍጠው ሠርቶ ማሳየት ነው ተገቢው። ሌላው ደግሞ እንደፎከሩት ቢፃፍም በቃ አለቀ ደቀቀ የኢሕአፓ ታሪክ እርሶና ጓደኞቾ በፃፉት ተደምድሟልና አበቃለት ማለት አይደለም። ሌላው ጭማሪ ከማብቃቴ በፊት እውነት ልንገርዎትና አቶ እያሱ ያሰቡት መጽሐፍ እከሌ አንጃ፣ እነከሌ አንጃ፣ እነከሌ ወያኔ ከማለት የዘለለ እንደማያስነብቡን እኔኛ አላውቅም ይታየኛል።

"ፀብ ያለሽ በዳቦ እንዲሉ" ሁሉም ቢዘጋዎ በትንሹም ቢሆን ስለ ኢሕአፓ የአቅማቸውን የሚበረክቱትን መደብደብ አሳፋሪ ነው። ሁሉንም አባረውና ሸኝተው የድርጅቱን ጣራና ግርግዳ ታቅፈው አጠገብዎ የሚነድፉት ቢያጡ እንደ ሥራ ፈት እብድ ከላይ እታች ከራሶ ይላተማሉ። የቀረቀሮትንና የዘጋዎትን ሁላ እርሶ እንደሚሉት አንጃ-ወያኔ-አንጃ ተሆኖ ሳይሆን ዓመሎ ነው። የማጥላላት አባዜ ተጠናውቶት "ገበያው ደርቷል መሰል ስለ ኢሕአፓ ፀሐፊው ምነው በዛ" ይላሉ። ከተረዱት በተለይ የእህታችን ሕይወት ተፈራ መጽሐፍ

የአሁኑን አዲስ ትውልድ ስለ ኢሕአፓ እንዲያነብ አድርጎታል። ተከትሎ የወጣው "የአሲምባ ፍቅር" ገና ከጅምሩ በ10 ሺዎች በሰልፍ ነው የተሸጠው። በተደጋጋሚም ታትሟል። ያብዱ ይሆናል እንጂ የአቶ አስማማው ኢ.ሕአሠ ቁጥር ሁለት በጉጉት እየተጠበቀ ነው። የወ/ሮ ቆንጂት ምርኮኛ ወደ ፊልም ቀረፃ ተሸጋግሯል። እንግዲህ ያራሉ፡ ይደብናሉ እንጂ ሌላ ምን ያመጣሉ? ይህ የሚያሳየው በኅብረተሰቡ ዘንድ ታምቆ ያለው ስለ ኢ.ሕአፓ ማንበብና ስለ ኢ.ሕአፓ የማወቅን ጉጉት ነው። ይህ ሊያስደስት ይገባል። የለም ሞቷል የሚባለው ኢ.ሕአፓ ከላይ እንደጠቀስኩት የሀሳብ ፓርቲ ሆኖ በሰዉ ልቦና ውስጥ መኖሩን ነው። ሀገር ቤት በሚወጡ መጽሔቶች ስለ ኢ.ሕአፓ ጥሩም መጥፎም ይፃፋሉ። መጥፎ ለሚጽፈው፡ አይደለም ብሎ ሌላው ምላሽ ይሰጣል። እንደውም አሁን አሁን መጽሔቶቹ ማሻሻጫቸው ስለ ኢ.ሕአፓ ጽሁፍ ይዘው ከወጡ ገበያው ይደራል። ለምን? ታሪክ ያለው ፓርቲ ስለሆነ። የኢ.ሕአፓ ታሪክ ውቅያኖስ በጭልፋ እንዲሉ ገና ያልተፃፈና ብዙ አጓጊ ስለሆነ። እና ይህ ደስ አያሰኝም? ስለ ኢ.ሕአፓ ማንበብ የሚፈልግ አዲስ ትውልድ ከ36 ዓመት በኋላ ብቅ ሲል? እርሶ ካልሠሩት፤ ክሬዲቱ ለእርሶ ካልሆነ እንዴት? እውነት እውነት እሎታለሁ አኬሩ አልፎቦታል።

ይህ ጽሑፍ ፀበል ሆኖት ከያዞት ንድፊያ ይገላግሎት ዘንድ እየተመኘሁ በዚሁ ይበቃ ይመስለኛል። ካልተሻሎት እኛም ኢ.ሕአፓዎች ነንና ምላሻችን ይቀጥላል። "ዓሣ ጎረጎረ ዘንዶ አወጣ" እንዳይሆን!

የአቶ እያሱ ዓለማየሁን ጽሁፍ "ኢ.ሕአፓና ታሪኩ" ካላነበባችሁ ከታች ባለው Link ማግኘት ትችላላችሁ።

http://www.assimba.org/Articles/EPRP_and_Its_History.pdf

ሰላም እንክረም

ጉዱ ካሣ gudukassa2014@gmail.com